# ጭቆናን ለማስወገድ የሚረዱን መመሪያዎች

## The Checklist for Ending Tyranny

**Peter Ackerman and Hardy Merriman**

From the book: Is Authoritarianism Staging a Comeback?
Editors: Matthew Burrows and Maria J. Stephan
The Atlantic Council, Washington, DC — 2015
Translation: JD Gebre Abebe Gellaw, June 2018

# TRANSLATOR’S NOTES

Please insert any helpful information about this translation here.

## ጭቆናን ለማስወገድ የሚረዱን መመሪያዎች

### በፒተር አከርማን እና ሃርዲ ሜሪማን

### ትርጉም እንግዱ ወልዴ / አርታኢ አበበ ገላው

በዘመናችን በዓለም ላይ እጅግ ደም አፋሳሽ ግጭቶች እየተከሰቱ ያሉት በሃገራት መካከል ሳይሆን በየአገሮቹ ባሉ ጨቋኝ አገዛዞችና በተጨቋኙ ሰፊው ሕዝብ መካከል ነው። በሰፊው እንደሚታመነው የተጨቆነ ሕዝብ ሁለት አማራጭ አለው፥ አንድም ጭቆናው ይቀንሳል በሚል ተስፋ ጨቋኙንና ጭቆናውን ተቀብሎ መኖር ወይም ሃይል የተቀላቀለበት አመጽ በማካሄድ ነጻነትን መጎናጸፍ። ይህ ውስን የሆነ ጭቆናን የማስወገጃ ምልከታ ግን ትክክል ላለመሆኑ በተደጋጋሚ የተደርጉ ግን ትኩረት ያልተሰጣቸው ህዝባዊ ንቅናቄ ዘመቻዎች (አንዳንድ ግዜ የ“ሕዝባዊ ሃይል” ንቅናቄዎች ወይም “ሃይል አልባ” ግጭቶች በመባል የሚታወቁት) ማስረጃዎች ናቸው። ከ እ.ኤ.አ. 1900 ጀምሮ በአማካይ በዓመት አንድ ትልቅ የሆነ ህዝባዊ አመጽ በስልጣን ላይ ባለ አገዛዝ ላይ ይደረጋል።[1] እነዚህ በዜጎች የሚመሩ ንቅንቄዎች ከ1972 ጀምሮ በተከሰቱና ወሳኝ በሚባሉ የጂዎ-ፖለቲካ (geopolitical) ግጭቶችና ዲሞክራሲያዊ ሽግግሮች ላይ ተጽዕኖ አሳርፈዋል።[2] ሆኖም ግን የፖሊሲ አውጪዎች፣ ምሁራን እንዲሁም ጋዜጠኞችና አንዳንድ ጉዳዩን የሚከታተሉ ሰዎች ይህን ዜጎች ሃይል አልባ በሆነ መንገድ ጭቆናን በማስወገድ ነጻነትን ሊጎናጸፉ የሚያስችላቸውን አቅም አቃለው ሲመለከቱ ይታያሉ።

### ህዝባዊ አመጾች ቀድመው ያለመተንበያቸው ጉዳይ

በ 2011 በቱኒዚያና በግብጽ የተደርጉ አመጾች እንዲሁም በ 2014 በዩክሬን የተደረገው አመጽ በታችኛው እርከን ላይ ያሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚያደርጉት ሕዝባዊ አመጽ ያለው ለውጥ የመፍጠር አቅም በራሱ በአመጽ አድራጊው ህዝብ ዘንድ አግራሞትን ጭሯል። ማንም እነዚህ አመጾች ይመጣሉ ብሎ የጠበቀ አልነበረም። በ 2000 በሰርቢያ፣ በ 2003 በጆርጂያ በ 2004 በዩክሬን የተደረጉት “የቀለም አብዮቶች” ይመጣሉ ብለው የጠበቁት ትቂቶች ብቻ ነበሩ። ከነዚህ አብዮቶች አስር ዓመት ቀደም ብሎ የፊሊፒንሱ ፈላጭ ቆራጭ ፈርዲናንድ ማርቆስ (1986)፣ የቺሊው አውጉስቶ ፒኖቼ (1988)፣ በፖላንድ የነበረው የሶቭየት አገዛዝ (1989)፣ ወይም በደቡብ አፍሪካ የነበረው የአፓርታይድ አገዛዝ (1992) ሃይል አልባ (ሰላማዊ) በሆነ ትግል ይውድቃሉ ብሎ የገመተ አልነበረም።

የዓለም አቀፍና የአካባቢ ተንታኞች ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎች ሰላማዊ ትግሎች ስኬታማ የሆኑበትን ምክንያት ለማስረዳት ሲቸገሩ ይታያሉ። አብዛኛውን ግዜም ውጤታማ የሆኑት ህዝባዊ አመጾች በየሃገሩ ባሉ በተለዩ ሁኔታዎች የመጡ በታሪክ ያልተለመዱና ለየት ያሉ ናቸው ብለው ይደመድማሉ። ምክንያቱም ውጤታማ የሆኑትን ትግሎች ሂደታቸውን ለየት ያለ አድርጎ ማየት እንጂ ስልታዊ በሆነ እንቅስቃሴ ህዝቡ በጨቋኞች የበላይነት እንደተጎናጸፈ አይቀጥሩም። በዓለም ዙሪያ ያሉ ጨቋኞች ግን ትግሎቹ ውጤታማ የሆኑበትን መንገድ ጠንቅቀው ያውቃሉ። የህዝባዊ ሃይል ንቅናቄዎችም የአገዛዛቸውን እድሜ የሚያሳጥሩ እንደሆኑ ይገነዘባሉ።

ሃይል ባልባ ግጭት (ሰላማዊ ትግል) ባለፉት አስር አመታት እየጨመረ በመምጣቱ ዲሞክራሲያዊ ለውጥን የሚደግፉ ወገኖች ህዝባዊ ንቅናቄዎች ለምን ውጤታማ ሆኑ የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤ ማሳደግ አለባቸው። ሃይል አልባ ትግል በብዙ ሁኔታዎች ውስጥ ሲሰራ ይታያል ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሁለት መሰረታዊ እውነታዎች ናቸው። አንደኛው ምክንያት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች ስልጣን ይዘው ለመቆየት መጠነ ሰፊ የሆነ የህዝቡ ታዛዥነት ያስፈልጋቸዋል። ተያያዥ የሆነው ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ለአገዛዙ ታዛዥና ታማኝ ያልሆኑና የማይፈልጉ ሰዎችም መኖራችው ነው።

### ህዝባዊ አመጾች እንዴት ይተገበራሉ?

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት እውነታዎች መሰረት የህዝባዊ አመጹ መሪዎች ህዝቡን ለአድማ፣ ለተአቅቦ ዘመቻ፣ ለተቃውሞ ሰልፍና ለሌሎችም የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በማነሳሳት ህዝቡ በዘዴ ለአገዛዙ ታዛዥነቱን እንዲነፍግና ለጭቆና የተዘረጋውን ስርዓት በማናጋት መብትን፣ ነጻነትንና ፍትህን ይጎናጸፋሉ። ህዝቡ በህዝባዊው ንቅናቄ ላይ የሚያደርገው

© 2014 Peter Ackerman and Hardy Merriman

ተሳትፎ ሲስፋፋና ሲያድግ የአመጹ መሪዎች ላይ የሚደረገው ጫና ትግሉን ለማስቆም በቂ አይሆንም፤ እንደውም የበለጠ ትግሉን ያቀጣጥለዋል።

አመጹና መስተጓጎሉ ሲቀጥል በመንግስት ውስጥና በሌሎችም ለአገዛዙ ወሳኝ በሆኑ ተቋማት (በፖሊስ፣ በጦር ሰራዊት፣ በአግዛዙ መገናኛ ብዙሃን፣ እንዲሁም በፖለቲካ፣ ቢሮክራሲና የኢኮኖሚ መዋቅሮች ውስጥ) መሰነጣጠቅ መታየት ይጀምራል። እነዚህ መሰነጣጠቆች አብዛኛውን ግዜ አንዳንድ ባለስልጣናትን ስርአቱን እንዲከዱ ያደርጋል፣ ክደቱም ከላይ ወደታች ይዛመታል። ይህም ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን ለማስቀጠል መመኪያ የሆኑትና በቁሳዊ ሐብት፣ በሰው ሃይል፣ በሰዎች ክህሎት፣ እውቀትና በመረጃ ላይ የነበረን ተቆጣጣሪነት፣ እንዲሁም በሰዎች ላይ እገዳ የመጣል አቅምን ስርዓቱ እንዲያጣ ያደርጋል። ትዕዛዛቸውን የሚያስፈጽሙበት የስልጣን ተዋረድ ሲጠፋና አማራጭ ሲያጡ ቀጣይነት ባለው መልኩ ሲካሄድ የቆየው ህዝባዊ ትግል አገዛዞቹን ከያዙት ወንበር ያነቃንቃቸዋል። አብዛኛውን ግዜም ሂደቱ ወደ አጠቃላይ ለውጥ ያመራል።

## ክህሎቶችና ነባራዊ ሁኔታዎች

ህዝባዊ አመጾች እየጨመሩና ተጽዕኖቸውም እያየለ በመምጣት ላይ ይገኛል። በመሆኑም የትግሉን ዉጤት የሚወስኑትን ምክንያቶች መመርመር እጅግ አስፈላጊ ነው። ህዝባዊ አመጹ ከመጀመሩ በፊት ያሉት ቅድመ ሁኔታዎች ህዝባዊ አመጹ ወይም ጨቋኝ አገዛዙ አሸናፊ እንዲሆኑ ያደርጋሉ? ወይንስ ድሉ የሚወሰነው ህዝባዊ አመጹም ሆነ አገዛዙ በሚጠቀሙበት ስልትና ክህሎት ነው?

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጆች አባል የሆኑበት አለማቀፍ ሃይል አልባ ግጭት ማእከል (International Center on Nonviolent Conflict) ዋና ተልዕኮ የህዝባዊ አመጽን ሂደትና ውጤት የሚወስነው ጥቅም ላይ በሚውለው ክዕሎት እንጂ በሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች አይደለም የሚል እምነት አለው። ይህ አቋም በተለይ አገዛዞች ሃይል በሚጠቀሙባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ችግር ይገጥመዋል። “ሃይል አልባ ትግል የሚሰራው ሃይልን በማይጠቀሙ (ወይም ቢጠቀሙም እጅግ በጥቂቱ) አገዛዞች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ነው” የሚል ምክንያትም ይቀርባል። ነገር ግን ይህ መከራከሪያ በደቡብ አፍሪካ የተሸነፈውን የአፓርታይድ አገዛዝ፣ ወይም ደግሞ ፒኖቼ በቺሊ፣ ማርቆስ በፊሊጲንስ እንዲሁም በፖላንድ የኮሚኒስት ስርዓት እንዴት እንደተገረሰሱ ይዘነጋል። በቅርብ ከነበሩት ደግሞ ሆስኒ ሙባረክን ከግብጽ፣ ቤን ኣሊን ከቶኒዚያ መጥቀስ ይቻላል። እነዚህ የተዘረዘሩት አገዛዞች እጅግ ሃይለኛ ሃይልን የማይጠቀሙ ስርዓቶች ናቸው ብሎ ማመን ወይም ቢጠቀሙ እንኳ በጥቂቱ ብቻ ነው ብሎ ማለት አስቸጋሪ ነው።

እነዚህ ምሳሌዎችን በአሃዝ በተደገፈ ትንተና ማሳየት ይቻላል። ፍሪደም ሃውስ (Freedom House) የተሰኘው ድርጅት በ2008 ባሳተመው ጥናት ከፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች የተላቀቁ 64 አገሮች ባደረጓቸው ህዝባዊ አመጾች ላይ የነበሩትን መዋቀራዊ ሁኔታዎችና በትግሉ ላይ ያደረሱትን ትጽዕኖ መርምሯል። ጥናቱ ከደርሰባቸው መደምደሚያዎች ውስጥ ይህን እንመልከት፣

> ...በጥናቱ የተመረመሩ ፖለቲካዊ ወይም አካባቢያዊ ሁኔታዎች በህዝባዊ አመጹ ስኬት ወይም ውድቀት ላይ ምንም አይነት ተጽዕኖ አላሰደሩም... በድህነት በተጎሳቆሉ አገሮች የሚደረጉ ህዝባዊ ንቅናቄዎች ልክ በሃብታም አገሮች እንደሚደረጉት ሁሉ የመሳካት ዕድላቸው ተመሳሳይ ነው። ጥናቱ በተጨማሪም የዘውግ ወይም የሃይማኖት ፉክክር ባለባቸው አገሮች እንኳ አንድ የሆነና የተጠናከረ ህዝባዊ ተቃውሞ ለመፍጥር ችግር የታየበት ሁኔታ እንዳልነበር ያሳያል። የአገዛዙ አይነቶችም ቢሆን ህዝባዊ ንቅናቄው በሚያገኘው ድጋፍ ላይ ተጽዕኖ እንዳላሳደሩ ጥናቱ ጠቁሟል።[3]

በጥናቱ እንደታየው በህዝባዊ ንቅናቄና አመጾች መፈጠርና ሒደት ላይ ትርጉም ያለው ተጽዕኖ ያለው ሆኖ የተገኘው የመንግስት ማዕከላዊነት ነው። የጥናቱ ጸሃፊዎች እንዳስቀመጡት፣

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

> ጥናቱ እንደሚመክረው ከፍተኛ የሆነ ማዕከላዊ አሰራር በሰፈነበት ስርዓት ጠንካራ የሆነ ህዝባዊ ንቅናቄ ለመፍጠርና ስርዓቱን ለመገዳደር አመቺ ነው። በተቃራኒውም ቢሆን ከፍተኛ የሆነ ኢ-ማዕከላዊ የሆነ አስተዳደር ያለው ስርዓት ውስጥ ውጤታማ የሆነ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለማስነሳት አስቸጋሪ ይሆናል።[4]

በመሆኑም ጥናቱ አንድ አካባቢያዊ ተጽዕኖ በትግሉ አቅጣጫ ላይ ተጽዕኖ እንዳለው ቢያስቀምጥም፣ አጠቃላይ የጥናቱ ግኝት ግን አካባቢያዊ ሁኔታዎች ለትግሉ እንቅፋት ይሆናሉ የሚለውን ውድቅ አድርጓል።

ከሶስት ዓመት በኋላ ተሸላሚ በሆነውና በ2011 በተጻፈው፥ *Why Civil Resistance Works: The Strategic Logic of Nonviolent Conflict*, Erica Chenoweth and Maria Stephan *(ሕዝባዊ አመጽ ለምን ውጤታማ ይሆናል? የሃይል አልባ ትግል ስልታዊ ተጠየቅ)* በተባለው መጽሃፋቸው ኤሪካ ቼንወት እና ማሪያ ስቴፋን 323 የሚሆኑና ከ1900 እስከ 2006 የተካሄዱ ሃይል አልባና ሃይልን የተጠቀሙ በስልጣን ላይ ያሉ መግስታትን የተገዳደሩ ትግሎችን ዳሰዋል።[5] በጥናቱም አዲስ ግኝት መሰረት ሃይል አልባ ትግሎች 53% ያህሉ ግዜ ስኬታማ ሲሆኑ ሃይልን የተጠቀሙት ትግሎች ደግሞ 26% ግዜ ብቻ ስኬታማ ሆነዋል።[6] ጥናቱ በተጨማሪ እንዳሳየውም የአገዛዙ ጭቆናና መዋቅራዊ ሁኔታዎች በትግሉ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ቢችሉም (በአብዛኛው ተጽዕኖው ከሚገመተው በታች ቢሆንም - በጥናቱ መሰረት ሃይልን የሚጠቀሙ አገዛዞች የትግሉን ውጤት የመቀነስ አቅማቸው ወደ 35% ነው) ምንም አይነት መዋቅራዊ ሁኔታዎች በትግሉ ውጤት ላይ ወሳኝ ተጽዕኖ አላሳደሩም።[7] ጥናት አድራጊዎቹ የሰበሰቡትን መረጃ በሚገባ ከፈተሹ በኋላ "ሰዎች ለሃይል አልባ ትግል መክሸፍ ተጠያቂ የሚያደርጓቸው አካባቢያዊ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው ህዝባዊ ንቅናቄዎች ግን ብዙ ግዜ ስኬታማ እንደሚሆኑ ደምድመናል" ብለዋል።[8]

እነዚህ የጥናት ውጤቶች የሚያሳዩት ህዝባዊ አመጽን በተመለከተ በተለምዶ ያለው አስተሳሰብ ትክክል እንዳልሆነ ነው። ለሰላማዊ ትግሉ ውጤታማነት ወሳኙ ክህሎትና ጥቅም ላይ የዋለው ስልት እንጂ ሌሎች ሁኔታዎች አይደሉም። ጭቆናን የሚታገሉ አካላት የመጀመሪያው በስልት ላይ የተመሰረት ውሳኔያቸው እንዴት እንታገል የሚለው መሆኑን ስንገነዘብ የጥናቱ ውጤት የሚገርም አይሆንም። አካባቢያዊ ሁኔታዎች የትግሉን ውጤት የሚወስኑ ቢሆን ኖሮ የሚመረጠው የትግል ስልት አይነት ወሳኝ አይሆንም ነበር፤ እንዲሁም በሰላማዊና ሃይልን በሚጠቀሙ ትግሎች መካከልም የውጤት ልዩነት አይኖርም ነበር።

የጥናቱ መረጃ ግን የሚያሳየው ያንን አይደለም። ከ 1900-2006 የነበሩ ህዝባዊ ንቅናቄዎች ውጤታማነታቸው በእጥፍ ጨምሯል፣ የቅርብ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ደግሞ የህዝባዊ ንቅናቄዎች አሁንም ውጤታማ የመሆናቸው እድል ብዙ አልተቀየረም።[9] የሰላማዊ ትግል አድራጊዎች የሚያሸንፉትን ትግል ብቻ ነው የሚያደርጉት ሲሉ አንዳንዶች ከላይ የተጠቀሰውን ሃቅ ለመከራከር ይሞክራሉ። የጥናቱ አድራጊዎች ግን ይህ መከራከሪያ እንደሚመጣ ያውቁ ስለነበር "....አብዛኛዎቹ ትግሎች የተደረጉት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች ባሉባቸው አገሮች መሆኑን ጠቁመው ፍጹም ሰላማዊ የሆኑ ተቃውሞዎች እንኳ ህይወትን ሊያስከፍሉ በሚችሉባቸው አገሮች ተከናውነዋል...." ይላሉ።[10]

የኖቤል ተሸላሚ የሆነው የምጣኔ ሃብት ባለሙያ ቶማስ ሼሊንግ ከሃምሳ ዓመት በፊት በጻፈውና *Civil Resistance as a National Defence: Nonviolent Action against Agression* በተባለው መጽሃፉ የሚከተለውን ድምዳሜ አስፍሯል፦

> ጨቋኙና ተጨቋኙ ህዝብ አብዛኛውን ግዜ በእኩል ተፋጠው ይገኛሉ። ተጨቋኞች በስነምግባር የታነጸ አደረጃጀት ካላቸውና ከጨቋኞች ጋር ላለመተባበር ከወሰኑ ጨቋኙ የሚያስፈልገውን ብዙ ነገር ሊነፍጉት ይችላሉ።

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

© 2014 Peter Ackerman and Hardy Merriman

> በተመሳሳይም ጨቋኙ በእጁ የሚገኘውን ሃይል በመጠቀም ህዝቡ የሚፈልገውን አብዛኛውን ነገር ሊከለክል ይችላል። ሁኔታው የድርድር መልክ ስላለው ስነምግባርና የሚከተለውና በደንብ የተደራጀው ወገን ሌላው የሚፈልገውን አብዛኛውን ነገር መንፈግ ይችላል፤ አሸናፊውም የሚታይ ይሆናል።[11]

ሼሊንግ እንደሚለው የህዝባዊ እንቢተኝነት አራማጆችም ሆኑ ጨቋኝ አገዛዙ የሚጠቀሙበት ክዕሎት ዋጋ (ወጪ) ሊይስከፍልም ሆነ ጠቀሜታ (ትርፍ) ሊኖረው ይችላል። አሸናፊ ሆኖ የሚውጣው ወጪውንና ትርፉን አስልቶ የሚመጣው ነው። በክዕሎት የታጠቀ የህዝባዊ እምቢተኝነት መሪ ቀውስ እንዲፍጠርና አገዛዙን የሚያገለግሉ ሰዎች ክህደት እንዲፈጽሙ መንገድ ይከፍታል። እንዲሁም መጠነኛ ቀውስን ብቻ በመጠቀም ብዛት ያላቸው የአገዛዙ አገልጋዮች እንዲከዱ ያደርጋል። በተመሳሳይም ክዕሎትን የሚጠቀም ጨቋኝ አገዛዝ ህዝቡ ተገዢ እንዲሆን ሃይልን ይጠቀማል፤ በተቻለ መጠንም ጥቂት ሃይልን በመጠቀም ከፍተኛ ተገዢነትን ለማስፈን ይጥራል። ተገዢዎቹ በአገዛዙ ላይ የከሃጂዎች ቁጥር እንዲጨምር የሚያደርጉት ጥረት በአንድ በኩልና  አገዛዙ ለማስፈን የሚጥረው የታዛዥነት (ተገዢነት) መጠን በሌላ በኩል ተነጻጽሮ የበለጠ ውጤት የሚያስመዘግበው አሸናፊ ይሆናል።

## ጭቆናን ለማስወገድ  የሚረዱን ሶስት መንገዶች

በህዝባዊ እንቢተኝነት ትግል ውስጥ የሚውሉት ስልቶችና ክዕሎቶች ለሚገኘው ውጤት ወሳኝ ናቸው ካልን በተለያዩ የትግል ወቅቶች ጥቅም ላይ የዋሉና ውጤታማ የሆኑ ክዕሎቶችን፣ የተለዩ ችሎታዎችንና፣ ትግሎቹ ይተከተሏቸውን አማራጮች መለየትና መመልከት አለብን። በአንድ ውጤታማ ትግል ውስጥ ያሉ የተለያዩና  ብዙ ጉዳዮችን መመልከትና መተንተን ይቻላል። አጣርተን ስንመለከት ግን ለውጤታማ ህዝባዊ እንቅስቃሴ አስፈላጊዎቹ ሶስት ነገሮች ሆነው እናገናቸዋለን፣

1. ህዝቡን አንድ የማድረግ ችሎታ
2. የንቅናቄው እቅድ
2. የሃይል አልባ ትግል ስነ ምግባር ናቸው

ከላይ የተጠቀሱ ሶስት ነገሮች ህዝባዊ ትግል ውስጥ ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት ለትግሉ ውጤታማነት ወሳኝ ለሆኑ ሌሎች ሶስት ጉዳዮች መከሰት ሆኔታዎችን ያመቻቻል፣

እነዚህም፥

1. በህዝባዊ እንቢተኝነቱ የሚሳተፉትን ሰዎች ቁጥር መጨመር
2. ጭቆናው የሚያስከትለውን ተጽዕኖ መቀነስና እንደውም ጭቆናው መልሶ ስርዓቱ የሚጎዳ እንዲሆን ማድረግ
3. ስርዓቱን የሚከዱ አገልጋዮችን ቁጥር መጨመር ናቸው

እነዚህ ሶስት ነገሮች ትግሉን በምናካሂድበት ወቅት መዘንጋት የሌለብን ጉዳዮች ናቸው። እነዚህን ሶስት ነገሮች ከተከተልን ትግሉ ውጤታማ ይሆናል ብለን እናምናለን። ነገር ግን እነዚህ ሶስት ነገሮች ብቻ ለውጤት የሚያበቁ ቀመሮች ናቸው ብለን አናምንም። ትግሉ መስመር እንዲይዝና ትግል አድራጊው ህዝብ ሃሳቡን የተደራጀ እንዲያደርግ፣ ትግሉንም ለውጤት እንዲበቃ ይረዳል ብለን እናምናለን።

የእነዚህ ሶስት ነገሮች አንዱ ተግባር በትግሉ ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ ግራ መጋባቶችን ማስወገድ ነው። በህዝባዊ አመጽ ወቅት አንዱ ችግር የሚሆነው የትግሉ ውስብስብነት ነው። በዚህ ውስብስብ ዳመና ውስጥ ውሳኔዎችን ለመወሰንና ምን ሁኔታዎች በውሳኔ አሰጣጡ ወቅት መጤን እንዳለባቸው ለማወቅ አስቸጋሪ ይሆናል። አንድ የሙብት አቀንቃኝ ወይም ሌላ

ይህ ምዕራፍ በ Mathew  Burrows  and  Maria  J.  Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging  a  Comeback?, Washington,  DC: The  Atlantic Council,  2015.  ታትሞ ወጥቷል።

© 2014 Peter Ackerman and Hardy Merriman

ከውጪ ሆኖ ትግሉን የሚታዘብ ሰው የትግሉ የወደፊት እጣ ለመተንበይ ከፈለገ ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት ሁኔታዎች በማጤን የትግሉን ወቅታዊ ሁኔታ፣ ጥንካሬውን፣ ደካማ ጎኑን እና ለውጤት የመብቃት ዕድሉን ለመገምገም ይረዳዋል።

ሁሉንም ነጥቦች ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን።

**1. ህዝቡን አንድ የማድረግ ችሎታ**

ጨቋኝ አገዛዞች ህዝቡን ከፋፍሎ በመግዛት ረገድ ከፍተኛ ልምድና ችሎታ ያካበቱ ናቸው። እነሱን ያሚታገሉ የህዝባዊ አመጽ አድራጊዎች ደግሞ ከገዢዎቹ የከፋፍለህ ግዛ ችሎታ የላቀ አንድነትን የመፍጠር አቅም ሊኖራቸው ይገባል። አንድነትን መፍጠርና ጠብቆ ማቆየት ብዙ ዘርፍ ያለው ስራ ነው። አንድነትን ለመፍጠር ዋናው ተግባር መሆን ያለበት ግን ህዝባዊ አመጽ አራማጆቹ የሚስማሙበት የጋራ ራእይ መፍጠር ወሳኝ ነው።

አንድነትን ለመፍጠር ሌላው ወሳኝ ጉዳይ ደግሞ ተቀባይነት ያለው አመራርና የአደረጃጀት መዋቅር መኖር ነው። በህዝባዊ አመጽ ውስጥ የሚደረግ ተሳትፎ በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው፤ በመሆኑም አመራር ላይ ያሎ ሰዎች በትግሉ ተሳታፊው ሰፊው ህዝብ ላይ የአዛዥነትና የቁጥጥር ስልጣን የላቸውም። ይህ ማለት በትግሉ ወቅት የሚደረጉ ውሳኔዎች ትግሉን በሚያካሂደው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ መሆን አለባቸው።

እያንዳንዱ ህዝባዊ ትግል አንድነትን ለመፍጠር የተለያየ መንገድ ሊከተል ይችላል። አንዳንዶቹ ከላይ ወደታች የሚወርድ አካሄድን ሲከተሎ ሌሎች ደግሞ ኢማዕከላዊ የሆነ አሰራር ሲጠቀሙ አንደገና ሌሎች ደግሞ ሁልቱን መንገዶች ቀላቅለው ይጠቀማሉ። የአንድ ንቅናቄ የአመራርም ሆነ ድርጅታዊ አወቃቀር ምንም ዓይነት ይሁን ንቅናቄዎች የተለያየ የአመራር ፎርም ይከተላሉ። አንድነት መኖሩ ደግሞ አመራሩና ሌላው የትግሉ ተሳታፊ ተናበው እንዲጓዙ ያደርጋል። ለእያንዳንዱ አገር አቀፍ የንቅናቄ መሪ በተዋረድ ያሉ በርካታ መሪዎች አሉ። እነዚህ በተዋረድ ያሉ መሪዎች ከተለያዩ ሌሎች ቡድኖችጋ ጥምረት የመፍጠር፣ ድርድር የማድረግና በየቡድኑ ያሉ የተለያዩ ፍላጎቶችን የማጣጣም ከፍተኛ ክህሎት ያላቸው እንዲሆኑ ያስፈልጋል።

ህዝባዊ ንቅናቄው ዘላቂ አንድነት እንዲኖረው በየደረጃውና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ መሪዎች ከፍተኛ የአመራር ችሎታ ሊኖራቸውና ተባብረው ይሰሩ ዘንድ ግድ ይላል።

የአንድነትን ጠቀሜታ በማስረጃ ለማየት በ 1980ዎቹ በደቡብ አፍሪካ የተደረገውን ህዝባዊ አመጽ መመልከት ይጠቅማል። የንጹህ ውሃና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሟሉ የሚጠይቁ በመቶ የሚቆጠሩ የሲቯል ቡድኖች ፈልቀው ነበር። እነዚህ ቡድኖች በጋራ ጉዳይ ላይ የፈጠሩት አንድነት በስተዋላ አፓርታይድን ለመጣልና አገራዊ እርቅ ለፍጠር ጠቅሟል። እነዚህ በኋላ (United Democratic Front) የዲሞክራሲያዊ አንድነት ግንባር ስር የተሰባሰቡ በታችኛው እርከን የሚገኙ የሲቪክ ቡድኖች ኢማዕከላዊ የሆኑ ታክቲኮችን በመጠቀም ለምሳሌ ጥቁሮች በየአካባቢያቸው ካሉ የነጮች ሱቆች እቃ እንዳይገዙ ተአቅቦ በመጥራትና በማስተባበር በተጓዳኝ ደግሞ ትላልቅ ከሆኑት አገራዊ ንቅናቄዎች ጋር ግኑኝነትና ትብብር በማድረግ የትግል አንድነትን መፍጠር ችለዋል።

**2. የንቅናቄው እቅድ**

ውጤታማ የሆነ ህዝባዊ ንቅናቄ ማድረግ ከሚገመተው በላይ ውስብስብ ነው። ህዝባዊ አመጽ ሲታሰብ ቀድሞ ወደ ሰዎች አይምሮ የሚመጣው የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ ነው። ነገር ግን ሌሎች ከመቶ በላይ የሚሆኑ ህዝባዊ አመጽን ማከናወኛ ዘዴዎች አሉ። እጅግ ውጤታማ የሆኑ ህዝባዊ አመጾች ምን ዓይነት ዘዴዎች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ፣ መቼ፣ የት፣

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

© 2014 Peter Ackerman and Hardy Merriman

እንዴት፣በማንላይና ማን እንደሚፈጽማቸው እንዲሁም ጥቅም ላይ ሊውል የታሰበው ታክቲክ ካሉት አማራጭ መንገዶች ውስጥ በየትኛው ደረጃ ላይ መፈጸም እንዳለበት በሚገባ ይገነዘባሉ።

ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ለመመለስ በዝርዝር ትንተናዎች ላይ የተመሰረተና በትግሉ ባላንጣዎች ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚዎችና አደጋዎች ላይ ያተኮረ ዕቅድ ማውጣትን ይጠይቃል። ከዚህ በተጨማሪም በትግሉ ላይ ተጽህኖ ሊኖራቸው የሚችሉ የአካባቢ ሁኔታዎች፣ ገለልተኛ ወይም ዳር ተመልካች ቡድኖችን ሁኔታ (የዓለም አቀፍ ማሕበረሰቡን ሁኔታ ጨምሮ) ይገመግማል። ከዚህ በመነሳት ህዝባዊ አመጾች የአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ግዜ ግቦችና ተዛማጅ ዕቅዶችን ያወጣል። እነዚህ ዕቅዶች እንደየአስፈላጊነቱ መሬት ላይ ያለው ሁኔታ እየታየ ሊሻሻሉ የሚችሉ ቢሆንም ዕቅዱን የመንደፍ ሂደትና በሰዎች ዘንድ መፈጠር ያለበት የአስተሳሰብ አንድነት ለትግሉ ተሳታፊዎች ከዕቅዱ ይበልጥ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው።

አጋጣሚ ሆኖ የክህሎትና የአካባቢ ሁኔታዎች መጋጨት ወይም አለመጣጣም በግልጽ የምናየው በአፈጻጸም እቅድ አወጣጡ ሂደት ነው። የአፈጻጸም እቅድ አወጣጡ መሰረት ንቅናቄው ከፊቱ የተደቀኑት ደጋፊም ሆነ ተጻራሪ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ናቸው። ክህሎትንና ስልታዊ አማራጮችን በመጠቀምም ንቅናቄው ደጋፊ ወይም ጠቃሚ የአካባቢ ሁኔታዎችን ለትግሉ እገዛ ጥቅም ላይ ሲያውል ተጻጻራሪና እንቅፋት የሆኑትን ደግሞ የሚወጣበትን ወይም የሚያስወግድበትን መንገድ ይፈልጋል።

የአፈጻጸም እቅድ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በፖላንድ የተካሄደው የሰራተኞች ንቅናቄ ነው።  ጥንካሬያቸውንና ያላቸውን አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ከባድ የሆነውንና የኮሚዩኒስት አገዛዙ እንዲያከትም ከመጠየቅ ይልቅ ፖለቲካዊ ተፈጻሚነቱ አስቸጋሪ ያልሆነውን ነጻ የሰራተኞች ማህበርን ለማቋቋም ጥሪ አቀረቡ። ሃይላቸውንም ሰራተኞችን በማደራጀትና በተለያዩ ሰራተኞች ዘንድ አንድነትን በመፍጠር ላይ አዋሉት። ይህንንም የተፈጠረ አንድነት በባላንጣቸው የኢኮኖሚ ደካማ ጎን ላይና ህጋዊ የበታችነት ላይ ተጠቀሙት። የአድማ ስልታቸውንም በመቀየር እንደ ቀደሙት ዓመታት በጎዳና ላይ ወጥቶ ተቃውሞ በማሰማት ለጠላት ጥቃት ከመጋለጥ ይልቅ እዛው በስራ ገበታቸው ላይ በመሆን አድማ ማድረግን ቀጠሉ። ሰራተኞቹም ገለልተኛ የሆኑ የሕትመት ውጤቶችን በመጠቀም ግንኙነታቸውን ለማቀላጠፍና በተለያዩ ከተሞች ባሉ ሰራተኞች ዘንድ ያለውን አንድነት አጠናከሩ። በስልታዊ መንገድ ዓላማን በማስፈጸምና (በስራ ቦታ ላይ እንዳሉ አድማ መምታትን ጨምሮ) በአቅማቸው መጠን በመንቀሳቀስ በፖላንድ የነበረው የሰራተኞች ንቅናቄ እንቅፋቶችን ሁሉ በመቋቋም ዲሞክራሲያዊ ፖላንድን እ.አ.አ. በ1989 ለመመስረት በቁ። [12]

### 3. የሃይል አልባ ትግል ስነ ምግባር

ለህዝባዊ ንቅናቄና ቀጣይነት ዋናው ቁልፍ ጉዳይ የትግሉ ተሳታፊዎች ትንኮሳ በሚፈጸምባቸው ወቅት እንኳ ፈጹም ሰላማዊ የሆነ መንገድን መከተላቸው ነው። ስነ ምግባርን የተላበሰ የሃይል አልባ ትግል የተሳታፊዎችን ቁጥር ለማብዛት፣ ጨቋኞች ትግሉን ለማፈን የሚከፍሉትን ዋጋ እንዲጨምር ለማድረግ፣ ጭቆናው መልሶ ጨቋኙ ላይ ችግር የሚፈጥርበትን እንዲሁም ከአገዛዙ ዋና ደጋፊዎች ከሆኑት ውስጥ ክህድት እንዲፈጽሙ ያበረታታል። የችኖወትና ስቴፋን ጥናት እንደሚያሳየው ከላይ የተጠቀሱት የሃይል አልባ ትግል ጠቀሜታዎች በጭቆና ላይ ድልን የመቀዳጀት ዕድሉን ከፍ ያደርጉታል።[13]

የሃይል አልባ ትግል ስነ ምግባርን እውን ለማድረግ ንቅናቄዎቹ ከአገዛዙጋ ለሚያደርጉት ትግል ህዝባዊ አመጽ ውጤታማ መንገድ መሆኑን መተማመን አለባቸው። ለዚህም ስለ ሕዝባዊ አመጽ ያሉ መረጃዎችና ታሪካዊ ማዕደሮችን ማጥናት ልክ ውጤታማ ስልትን እንደመጠቀም ሁሉ ሕዝባዊ አመጽን ውጤታማ ለማድረግ ጠቃሚ ናቸው። ንቅናቄዎች የሃይል አልባ ትግል ስነ ምግባርን ተፈጻሚ ለማድረግ የተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎችን መፍጠር ይችላሉ። ለምሳሌ በሰርቢያ ስሎባዳን ሚሎሶቪችን ከስልጣን ያሰወገደውና  የኦፑቶር ንቅናቄ በመባል የሚታወቀው ሕዝባዊ አመጽ አዲስ አባላትን ህዝባዊ አመጽ እንዴት እንደሚካሄድና ሃይል አልባ ትግልን ብቻ የማካሄድ አስፈላጊነት ላይ ስልጠና ይሰጥ ነበር።

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

እንዲህ አይነት ጥረቶች ትግሉ ሃይል አልባ ሆኖ የመቀጠሉ አስፈላጊነት ለክርክር እንዳይቀርብ ያደርጋሉ። ሰዎች እርስ በርሳቸው ስለ ሰላማዊ ትግል አስፈላጊነት አንዱ ሌላውን እንዲያሳምን ማድረግም አስፈላጊ ነው። ትግስት አለማድረግና በሕዝባዊ አመጹ እምነት ማጣት (በሶሪያ የተፈጸመውን አሳዛኝ ሁኔታ በማስታወስ) ብሎም ወደ ሃይል መጠቀም መሸጋገር ለአደገኛ ውጤት እንደሚያበቃ መገንዘብ ያስፈልጋል።

## 4. በህዝባዊ እንቢተኝነቱ የሚሳተፉ ሰዎችን ቁጥር መጨመር

በሕዝባዊ አመጽ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ብቸኛው የስኬት መለኪያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።[14] ለፈላጭ ቆራጩ አገዛዝ ታዛዥ የሚሆነው ቁጥር ሲቀንስ አገዛዙ እየተዳከመ ይመጣል፣ ሕዝቡን ተቆጣጥሮ ለመቆየት የሚያስፈልገው ወጪም ከፍተኛ ይሆናል። በተጨማሪም የተሳታፊዎችን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ጭቆናው መልሶ ጨቋኙን የሚጎዳበት ሁኔታ የፈጥራል የሚል እምነት አለን። ማስረጃዎችም እንደሚያሳዩት የንቅናቄው ተሳታፊዎች በከፍተኛ ደረጃ መጨመር የአገዛዙ ደጋፊዎች የሚከዱበትን ዕድል ይጨምራል።[15]

ከፍተኛ የህዝብ ተሳትፎን በምሳሌ ለማሳየት በ 2011 በግብጽና በቱኒዚያ የተደረጉትን እንመልከት። በሁለቱ አገሮች በተደረገው አብዮት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፈዋል። ወንዶች፣ ሴቶች፣ የተለያዩ እምነት ተከታዮች፣ እምነት የሌላቸው፣ ወጣቶች፣ በመካከለኛ እድሜ ላይ ያሉ፣ አዛውንቶች፣ በዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላይ የሚገኙ፣ የከተማና የገጠር ነዋሪዎች ተሳትፈዋል። በተቃራኒው በ 1989 በቻይና የነበረው የተማሪዎች ንቅናቄ እንዲሁም በ2009 በኢራን የነበረው አረንጓዴ ንቅናቄ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን አንቀሳቅሷል፣ የመገናኛ ብዙሃንን ትኩረትም ስቧል። ነገር ግን ሁለቱም ንቅናቄዎች ይተነሱበትን ዓላማ ከግብ አላደረሱም ምክንያቱም የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከማሳተፍ ይልቅ በተወሰኑ ክፍሎች ላይ በማተኮራቸው ነው።

በሕዝባዊ አመጽ ውስጥ ከፍተኛን ተሳትፎ መፍጠር የሚለው ጉዳይ የዚህ ጽሑፍ መነሻና ትኩረት ከሆኑት መመሪያዎች ይመነጫል። የሁሉም አንድ የሆነ ራእይ መኖር ለመቀራረብና ሕዝቡን ለትግል ለማነሳሳት ይጠቅማል። የእቅድ አፈጻጸም ፕላን መኖርም በትግሉ ተሳታፊዎች ዘንድ በራስ መተማመንን ከመፍጠር አልፎ የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ትግሉ የሚያስከትለውን ትጽዕኖ፣ ግዜ፣ መክፈል ስለሚችሉት መስዋትነት የበለጠ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳል። ውጤታማ የሆነ የትግል ስትራቴጂ (ዘዴ) በትግሉ ለሚሳተፉ ድሆች፣ ባለሃብቶች፣ ወጣቶች፣ አረጋውያንና ለሌሎችም ለትግሉ አስተዋጽዎ እንዲያደርጉ አማራጮችን ያመቻችላቸዋል። በትጥቅ የታገዘ ሃይል የአካል ጥንካሬ ያላቸውን ሰዎች ብቻ ሲያሳትፍ ሃይል አልባ ትግል ግን ሁሉም ትሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይሰጣል። በተጨማሪም ሃይል አልባ ትግል ብዛት ያለው ስብጥር ያለበት የሕብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ እንዲሆን ያበረታታል።

## 5. የጭቆናን ተጽዕኖ መቀነስና ጭቆናው መልሶ ጨቋኙን እንዲጎዳ ስለማድረግ

የፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች ዋናው መሳሪያ ጭቆናን የመፈጸም አቅም ነው። ውጤታማ የሆኑ ህዝባዊ ንቅናቄዎች ደግሞ ጭቆናው የሚያስከትለውን ተጽዕኖ እንዴት መቀነስ እንዳለባቸውና አገዛዙ ለጭቆናው የሚከፍለው ዋጋ የሚጨምርበትን መንገድ ይማራሉ። የህን ማድረጊያው አንዱ መንገድ ጭቆናው የሚያስከትለውን አደጋ ትክክለኛ በሆነ መንገድ መገምገምና ንቅናቄው ጥቅም ላይ የሚያውለውን ዘዴዎች በጥንቃቄ መምረጥ ነው። ምክንያቱም ሁሉም ዘዴዎች እኩል የሆነ የጭቆና ምላሽ ከአገዛዙ አያገኙም። ማዕከላዊነትን የተከተሉ እርምጃዎች ለምሳሌ እንደ የተቃውሞ ሰልፍ አይነቶች የመደፍጠጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ሲሆን፤ ማዕከላዊነትን ያልተከተሉ ዘዴዎች ለምሳሌ የገዢ ተአቅቦ፣ በቤት ውስጥ የመቀመጥ አድማ፣ ከትምህርት ቤት ሕመምን ምክንያት በማድረግ መቅረት፣ ወይም በአደባባይ ላይ ምልክቶችን ማሳየት አገዛዙ በቀላሉ ሊደፈጥጣቸው አይችልም። ምክንያቱም ለምሳሌ የእቃ ግዢ ተአቅቦን በተመለከተ ማን የተአቅቦው ተካፋይ እንደሆነ ለመለየት አስቸጋሪ ይሆናል፤ በቤት ውስጥ የመዋል አድማ ተስታፊዎችን ወይም በህመም ሰበብ ስራ የቀሩ ሰዎችን ለመለየት ፖሊሶች በየአንዳንዱ ሰው ቤት መዞር ሊያስፈሊጋቸው ነው። ይህ ደግሞ አስቸጋሪ ስራ ነው።

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

© 2014 Peter Ackerman and Hardy Merriman

በቺሊ በ1983 በነበረው ንቅናቄ የፖለቲካ ተቃዋሚዎች የአውጉስቶ ፒኖቼ አገዛዝ የሚያደርስባቸውን ጭቆና ለማስወግወድ ዘዴ መቀየስ ተገደው ነበር። ለአስር ዓመት ይተፈጸመው የጅምላ እስር ፣ ግድያ፣ ሰቆቃ፣ እና አፍኖ መሰወር ሰዎች ለመደራጀትና በጋራ ለመንቀሳቀስ ከፍተኛ ፍርሃት እንዲያድርባቸው አድርጓል። በዛን ዓመት ሚያዚያ ወር ከሳንቲያጎ ውጪ ያሉ የመዳብ አምራቾች ማሕበራት አድማ ጠሩ። ፒኖቼ ግን አድማው ከመጀመሩ በፊት ሰራዊቱን ወደ ቦታው በመላክ ደም እንደሚያፈስ ዛተ። በዚህ ግዜም የማህበራቱ መሪዎች የጠሩትን አድማ በመሳብ በአጠቃላይ አገሪቱ ይተቃውሞ ቀን አውጁ። በዚህ ተቃውሞም ህዝቡ ስራን በማጓተት፣ ቀስ ብሎ በመራመድ፣ ቀስ ብሎ በመንዳትና ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን ድስትና መጥበሻ በማንኳኳት ተቃውሞውን እንዲገልጽ ተደረገ።[16] በዚህ ተቃውሞም በርካታ ሰው መሳተፍ ችሏል። በየወሩም ተመሳሳይ ተቃውሞ ለማድረግ ተወሰነ። በዚህ ዓይነት ተቃውሞም ህዝቡ ፒኖቼ አንግሶት የነበረውን ፍራቻ ሰብሮ ለመውጣት ተቻለ። ይህ ዓይነቱ ተቃውሞም በተሳታፊዎቹ ላይ የሚያስከትለው አደጋ እጅግ ዝቅተኛና አገዛዙ ተቃውሞውን ለመደፍጠጥም አስቸጋሪ ሆኖበታል። የፒኖቼ ታጣቂዎች ለእንዲህ አይነቱ ሰፊ አድማስ ያለውና የተበታተነ የተቃውሞ ስልት መልስ አልነበራቸውም።

በተቃውሞ እንቅስቃሴ ላይ በአገዛዞች የሚደረግ የአፈናን መጠን መቀነስና ስርዓቱ ለአፈናው የሚከፍለውን መስዋትነት እንዲጨምር፣ እንዲሁም አፈናው መልሶ ስርዓቱን እንዲጎዳው ማድረጊያ ሌላው መንገድ ደግሞ አንዳንድ በህብረተሰቡ ዘንድ ያሉ ቅሬታዎችን ፖለቲካዊ ባልሆነ መንገድ ማቅረብ ነው (ለምሳሌ ስርዓቱ ስልጣን እንዲለቅ ከመጠየቅ ይልቅ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ወይም  የአካባቢ ጸጥታን የተመለከቱ ጥያቄዎችን ማቅረብ) የንቅናቄው መሪዎች አንዱ ሌላውን የሚተኩበትን ስርዓት መፍጠርና በተቃውሞ ተሳታፊዎቹና በሌሎች በአገር ዉስጥም ሆነ በውጪ ከሚገኙ ቡድኖችጋ ትብብር በመመስረት አገዛዙ የሚያደርሰው ጭቆና መልሶ እንዲጎዳው ሚጎዳው ማድረግ ነው። ለምሳሌ በ 2010 ግብጻዊውን አምደኛ ካሊድ ሰይድ በአገሪቱ ያለን ሙስና በማጋለጡ የጸጥታ ሃይሎች ከኢንተርኔት ካፌ አውጥተው ደብድበው ከገደሉ በኋላ ተቃዋሚው የፌስቡክ ቡድን "ሁላችንም ካሊድ ሰይድ ነን" በማለት የግብጽ መንግስት የካሊድን ህይወት ዋጋ ለማሳጣት ያደርገውን ሙከራ አጨናግፏል። የፊስቡክ ቡድኑ በተጨማሪም ሰይድ ማለት አብዛኛውን ግብጻዊ የሚወክል እንደሆነ ግልጽ በማድረጋቸው የግብጽ መንግስት የጭቆና ሙከራ መልሶ ራሱን እንዲጎዳው አድርገዋል።

**6. ብዛት ያላቸው ደጋፊዎች አገዛዙን እንዲከዱ ማድረግ**

ህዝባዊ አመጽ እያደገ ሲመጣ የአገዛዙ ደጋፊዎች መከዳት እየበረከተ ይመጣል። ለምሳሌ በስርዓቱ ውስጥ ባሉ ለውጥን በሚፈልጉ ሃይሎችና ስርዓቱን ማስቀጠል በሚፈልጉት መሃል ስልጣንን ለመቆጣጠር በይፋ ትግል ይካሄዳል። አገዛዙ ለኢኮኖሚ ፍላጎቱና የንግድ እንቅስቃሴ እንዲቀጥል ሲል ንቅናቄው የሚጠይቃቸውን ጥያቄዎች ያሟላል። ህዝባዊ ንቅናቄው ባነሳቸው ጥያቄዎች በማመንም ሆነ በስርዓቱ በመማረር ወይም የቤተሰብ አባሎቻቸው የትግሉ ተሳታፊ በመሆናቸው ምክንያት የሰራዊቱና የፖሊስ ዓባላት እንዲሁም በቢሮክራሲ ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች ታማኝነታቸውን ወደ ህዝባዊ ንቅናቄው ሊቀይሩ ይችላሉ። የአገዛዙ ደጋፊ የሆኑ ልሂቃን ሳይቀሩ ትግሉ ውጤታማ በሚሆን ግዜ የታሪክ ተጠያቂ ላለመሆን የስርዓቱን ቀጣይነት መጠራጠርና ገለልተኛ መሆን ይጀምራሉ።

በ2004 በዩክሬን በነበረው ብርቱካናማ አብዮት የተቃውሞ አስተባባሪዎች በጡረታ የተገለሉ የሰራዊት አባላትን እንደ አገናኝ በመጠቀም ከጸጥታ አስከባሪዎችጋ የግንኙነት መስመር ነበራቸው።[17] በግዜ ሂደትም ተቃዋሚዎች ፍጹም ሰላማዊና ምክንያታዊ መሆናቸውን በተግባር አስመሰከሩ፤ የጸጥታ ሃይሎችም የህብረተሰቡን ደህንነት እንዲጠብቁ ጥሪ አደረጉ፤ በህብረተሰቡ መካከልም ተራርቆ የነበረውን ግንኙነት ማህበራትን በመፍጠርና በተለያዩ መንገዶች አቀራረቡ (ለምሳሌ ለፖሊስ አባላት ጽጌረዳ አበባ በመስጠት)፤ በስርዓቱ የተፈሰጸመውን ሙስና አጋለጡ፤ በመጨረሻም ከስርዓቱ ጸጥታ ሃይሎች ዘንድ ድጋፍን አገኙ። አገዛዙ ተቃውሞውን ለመደፍጠጥ በሚሞክርበትም ግዜ ብዛት ያላቸው የሰራዊቱ አባላት ገለልተኛ ሆኑ። ይህ ክስተት በሚሎሶቪች ስር በነበረችው ሰርቪያም ተፈጽሟል። የሰራዊቱ አባላት ስርዓቱን ሳይከዱ በጦሩ ውስጥ እያሉ የሚመጣውን ትዕዛዝ አልቀበልም አሉ። አክቶበር 5 የኦፐቶር ንቅናቄ በጦዘበት ወቅት ከሄሊኮብተር

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

በቤልግራድ በተሰበሰበው ህዝብ ላይ የመበተኛ ኬሚካል እንዲያዘንብ የታዘዘው የፖሊስ አባል ትዕዛዙን አልፈጽምም አለ። ያቀረበውም ምክንያት አየሩ ጥሩ ስላልሆነ ሰዎቹ በደንብ አይታዩኝም የሚል ነበር። ቀኑ ግን ጥርት ያለ ጸሃያማ ነበር።በኋላ እንደተናገረው ግን ትዕዛዙን ያልፈጸመው የቤተሰቡ አባላት ከህዝቡ መሃል ሊኖሩ ይችላሉ ብሎ በመገመት እንደነበር ተናግሯል።[18]

በህዝቡ ንቅናቄ በማመንም ሆነ በግል ፍላጎት የተፈጸሙት ስርዓቱን የመካድ እርምጃዎች የህዝባዊ ንቅናቄው የረጅም ግዜ የስራ ውጤቶች ናቸው። ቀደም ብለው እንደተነሱት የዚህ ጽሁፍ ዋና ጉዳዮች ሁሉ  ስርዓቱን ደግፈው የያዙትን አካላት እንዲከዱ ማድረግ ከንቅናቄው አንድነት፣ የአፈጻጸም ዕቅድና ሃይል አልባ ስነ ምግባር የሚመነጭ ነው። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በህዝባዊ አመጽ ውስጥ የተሳታፊዎች ቁጥር በጨመረ ቁጥር ስርዓቱን የሚከዱት ሰዎች ቁጥር ይጨምራል። አንድነት፣ የአፈጻጸም ዕቅድና ሃይል አልባ ስነ ምግባርም ሁሉን አቀፍና ብዛት ያለው ተሳታፊዎችን ለመፍጠር ይረዳል። በተለይም ንቅናቄው በሃይል አልባ ስነ ምግባር የታነጸ ከሆነ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የስርዓቱ ደጋፊዎች እንዲከዱ ያበረታታል። ንቅናቄው ሰላማዊ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስና ወደ ሃይል እስካልተሸጋገረ ድርስ (በ2011 በሶርያ እንደተከሰተው አሳዛኝ ሁኔታ)፣ ትግሉ ለረጅም ግዜ የመቀጠልና የስርዓቱ ደጋፊዎችም እንዲከዱ የማድረግ ዕድል ይኖረዋል። የስርዓቱ ታማኞች በሃይል የሚመጣ ግልበጣ የማያሰጋቸው ከሆነ፣ የመክዳት ዕድላቸው የሰፋ ይሆናል፤ ይህም የአገዛዙን ሃይል ያመናምነዋል።

## ይህ ጽሁፍ ከህዝባዊ ንቅናቄ ውጪ ላሉ ያለው ጠቀሜታ

ይህ የመመሪያ ጽሁፍ  ጠቃሚነቱ ለተቃዋሚዎች ብቻ አይደለም። ሌሎች አካላትም ከአገዛዞችጋ ለሚደረግ ትግል ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ለምሳሌ ይህ የመመሪያ ጽሁፍ ጋዜጠኞች ህዝባዊ ተቃውሞን በተመለከተ በሚዘግቡበት ጊዜ ነገሩን በሚገባ ተረደው እንዲዘግቡ የረዳቸዋል። ጋዜጠኞው ጥልቀት ያለው ዘገባ እንዲያቀርብ በ 2014 በኪቭ አደባባይ በሞሎቶቭ ተቀጣጣይ ፈንጂ እየጋየ ያለውን ነገር ተጠግቶ እንዲያይ ማድረጉ የሚሰጠው ጥቅም እንደሌለ ይህ መመሪያ ግንዛቤ ያስጨብጣል። ነገር ግን የንቅናቄውን አንድነት፣ ዕቅድ፣ የሃይል አልባ ስነምግባር መጣሱን ለማወቅ፣ የተሳታፊዎችን ቁጥር መጨመር በተመለከተ፣ የጭቆናውን መቀነስ፣ የጸጥታ ሃይሎች ከአገዛዙ የሚወርደውን ትእዛዝ መቀበል ያለመቀበላቸውን ወዘተ የተመለከተ የተዋጣ የምርመራ ዘገባ ለማቅረብ ይህ ጽሁፍ እገዛ ያደርጋል። ተጨማሪ ምሳሌ ለመስጠትም የንግድ ማህበረሰቡ ለአገዛዙ ድጋፍ መንፈግ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ለመረዳት በየካቲት 21, 2014 የዩክሬኑ ፕሬዝዳንት ያኑኮቪች በህዝቡ ላይ ያደረሰው ጭፍጨፋ መልሶ በርሱ ላይ የበለጠ ቁጣን በንግድ ማህበረሰቡ ዘንድም መቀስቀሱን ሲረዳ በሰዓታት ውስጥ አገር ጥሎ መሸሹን መመልከት ጠቃሚ ይሆናል። እንዲህ አይነት ሁኔታዎችን ማጤን ጋዜጠኞች ስለ ህዝባዊ ንቅናቄ በሚዘግቡበት ግዜ ጠቃሚ ይሆናል።

ይህ ጽሁፍ በፖሊሲ አውጪዎች ዘንድ በ2011 አጋማሽ ላይ ታይቶ ቢሆን ኖሮ በሶሪያ በአሳድ አገዛዝ ላይ የተደረገው ህዝባዊ አመጽ የማሸነፍ ዕድል ይኖረው ነበር። በጦሩ ውስጥ የነበረው ስርዓቱን የመክዳት ሁኔታ (ከሱኒ ወታደሮች ውጪ ያሉት) ለድል ተቃሚ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በንግዱ ማህበረሰብ የነበረው ስርዓቱን ድጋፍ የመንፈግ ሁኔታም ሌላው ነው። ነገር ግን የ "ነጻ የሶሪያ ሰራዊት" የአሳድን የተረፉ አለዋየት ሰራዊት መዋጋቱን ማበረታታት ጠቃሚ እንዳልነበር መመልከት ይቻላል።

ይህ ጽሁፍ በተለይም በአንድ የተወሰነ አካባቢ ያሉና ለሚያካሂዱት አመጽ የሚረዳ የውጪ እገዛን ለሚሹ ንቅናቄዎች ጠቃሚ አሰራረ ለመቅረጽ ይረዳል። ለምሳሌ በመጀመሪያ የተጠቀሱት ሶስት ጉዳዮች (አንድነት፣ እቅድና ስነ-ምግባር) በከህሎት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው እነዚህን ለማጎልበት ከሌሎች ሃይሎችጋ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አስፈላጊ ነው። የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች አንቀጽ 19 መሰረት አገዛዞች ከአገር ውጪ የሚመጣን መረጃ ማገድ አይችሉም፣ ወይም ደግሞ መረጃውን ለተቃዋሚዎች የሚያስተላልፉ ዜጎችን መቅጣት አይችሉም። በዚህ ጽሁፍ ላይ የተነሱት ስድስቱም ጉዳዮች ለቴክኖሎጂ ፈጠራ መንገድ የሚጠቁሙ ሲሆን፣ ስድስቱንም ነገሮች ለማጎልበትም ቴክኖሎጂ ጠቃሚ ይሆናል።

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

© 2014 Peter Ackerman and Hardy Merriman

**በዚህ ጽሁፍ የተነሱ ስድስት ጉዳዮችና የነገ ዓለማችንን የሚወስኑ አመጾች/ግጭቶች**

የሃይል አልባ ትግል የሚካሄደው እጅግ ውስብስብ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ባሉበት ሁኔታ ከመሆኑ በተጨማሪ ትግሉን ከግብ ለማብቃት ከታችኛው እርከን ጀምሮ የሚደረግ ስልታዊ ቅንጅትና መናበብ ስለሚያስፈልግ ብዙ ግዜ ግራ መጋባት ሊፈጠር ይችላል። ጉዳዩ የነጻነትና የሰው ህይወት ጉዳይ እንደመሆኑም መጠን ንቅናቄዎቹ በሚወስዱት ውሳኔ ስህተት ላለመስራት በሚፈሩበት ግዜ አገዛዙ የሚፈልገው ሁኔታ ይፈጠራል። ይህም በአገዛዙ ዘንድ ያለመደፈር ስሜት እንዲኖር ያደርጋል።

በዚህ ጽሁፍ ላይ የተነሱት ጉዳዮች ተቃዋሚዎች በትግል ወቅት የሚፈጠረውን ብዥታ ለማስወገድና ወደፊት ለመራመድ ይጠቅማቸዋል። አንዳንዶች በዚህ ጽሁፍ ላይ የተነሱት ትግልን የማካሄጃ መመሪያዎች በጣም ቅለል ተደርገው የታዩና ወደፊት የሚደረጉ ህዝባዊ አመጾች በወቅቱና በቦታው ባሉ ሁኔታዎች የሚወሰኑ ናቸው ብለው ሊከራከሩ ይችላሉ።

ነገር ግን በዚህ ጽሁፍ ላይ ያሉ መመሪያዎች በተለዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚደረጉ ትግሎች እንደሚኖሩ አልካዱም። ይልቁንም ሁኔታዎቹን አጠቃላይ በሆኑ ስትራቴጂያዊ ማዕቀፎች ውስጥ እንድንረዳና ለምንና እንዴት ህዝባዊ አመጾች አሸናፊ ሆነው እንድሚወጡ ያሳያሉ። መመሪያዎቹን በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ያጠናው አቱል ጋዋንዴ እንዲህ ይላል፥

> መመሪያዎቹ ብዙ ልምድ ያላቸውን የህዝባዊ አመጽ ተሳታፊዎችን እንኳ ስህተት እንዳይሰሩ እንዲሁም ከውድቀት ይጠብቃቸዋል። መመሪያዎቹ በእውቀት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው ንቅናቄውን ከውድቀት ይጠብቃሉ። የማስታወስ፣ የትኩረት ማጣትና ሌሎች ችግሮች ለመፍታት ይረዳሉ። [19]
>
> ፍጹም ውስብስብ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ግዜና ችግሩን ለመፍታት የሚያስፈልግው እውቀት ከሰዎችም አቅምም ሆነ ከተከሰቱት ያልተጠበቁ ሁኔታዎች በላይ ሲሆን... [ውጤታማ መመሪያዎች] ቀላል ግን ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች እንዳይዘነጉ ይረዳሉ፤ መመሪያዎቹ ሰዎች እንዲወያዩና መጠነኛ የሆኑ ልዩነቶቻቸውን እንዲፈቱ እንዲሁም ወደፊት የሚከሰቱ ያልተጠበቁ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠር ይረዳሉ። [20]

መመሪያው የመጨረሻው አሸናፊ አገዛዙ ይሁን ወይም ህዝባዊ ንቅናቄው ቀድሞ መተንበያ አይደለም። ነገር ግን የዜጎች የነጻነት ጥያቄና ትግል ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞችን እንዴት ሊያስወግድ እንደሚችል ይጠቁማል።

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

© 2014 Peter Ackerman and Hardy Merriman

**ማጣቀሻ**

1. በ ቼኖዌት፣ ኤሪካና ማሪያ ስቴፋን ጥናት ላይ የተመሰረተ። ጥናቱ 105 የሚሆኑና ከ 1900 እስከ 2006 በተለያዩ አገራት የተካሄዱ ህዝባዊ ንቅናቄዎችን ተመልክቷል።
ቼኖዌት፣ ኤሪካና ማሪያ ስቴፋን (2011). ሕዝባዊ አመጽ ለምን ውጤታማ ይሆናል? የሃይል አልባ ትግል ስልታዊ ተጠየቅ። ኒው ዮርክ፣ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ። ገጽ 6.

Chenoweth, Erica, and Maria Stephan. 2011. Why Civil Resistance Works: The Strategic Logic of Nonviolent Conflict. New York: Columbia University Press. p. 6

ሙሉ መረጃውም ከዚህ በታች ባለው ማስፈንጠሪይ ላይ ይገኛል
NAVCO 1.1 data available at:
http://www.du.edu/korbel/sie/research/chenow_navco_data.html

2. ከ 1972 እስከ 2005 በነበሩ ወደ ዲሞክራሲ በተደርጉ 67 ሽግግሮች ላይ የተመሰረተና "How Freedom is Won: From Civic Resistance to Durable Democracy." (ነጻነት እንዴት ይገኛል፡ ከህዝባዊ አመጽ ወደ ዘላቂ ዲሞክራሲ) ከተባለው ጥናት ላይ የተወሰደ። የጥናቱ አድራጊዎች እንዳገኙትም፡

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

“ከ ስድሳ ሰባቱ፣ ሃምሳ በሚሆኑት ሽግግሮች ውስጥ ወይም ከ70 በመቶ በላይ በሚሆኑ አገራት ሽግግር ውስጥ ህዝባዊ አመጾች ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። በአገራቱም ሽግግሮቹ የተከሰቱት አንድም አምባገነናዊ አገዛዝ በማከተሙ አልያም አገራቱ በብሄር በመሰነጣጠቃቸው ነው። ህዝባዊ አመጽ ቁልፍ ሚና ከተጫወተባቸው ሃምሳ አገራት ውስጥ አንዳቸውም ነጻ አልነበሩም። ሃያ አምስቱ በከፊል ነጻ ሲሆኑ ሌሎቹ ሃያ አምስት አገራት ደግሞ ሙሉ በሙሉ ለጻ አልነበሩም። በ 2005 ከዓመታት በኋላ ሰላሳ ሁለቱ አገራት ነጻ ሲሆኑ፣ አስራ አራቱ ደግሞ በከፊል ነጻ ናቸው። አራቱ ደግሞ ፍጹም ነጻ አይደሉም።

Ackerman, Peter, and Adrian Karatnycky. 2005. How Freedom is
Won: From Civic Resistance to Durable Democracy. Washington,
DC: Freedom House. Pp. 6--7

3. ለህዝባዊ አመጽ ምቹ ሁኔታዎችና የዲሞክራሲያዊ ሽግግር ሂደት። የፍሪደም ሃውስ ልዩ ሪፖርት። ጁላይ 18, 2008. ገጽ 1.

Marchant, Eleanor, Adrian Karatnycky, Arch Puddington, and Christopher Walter. 2008. Enabling Environments for Civic Movements and the Dynamics of Democratic Transition. Freedom House special report. July 18. p.1

4. እንደላይኛው

5. ቼኖዌት፣ ኤሪካና ማሪያ ስቴፋን (2011). ሕዝባዊ አመጽ ለምን ውጤታማ ይሆናል? የሃይል አልባ ትግል ስልታዊ ተጠየቅ። ኒው ዮርክ፣ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ። ገጽ 6.

Chenoweth, Erica, and Maria Stephan. 2011. Why Civil Resistance Works: The Strategic Logic of Nonviolent Conflict. New York: Columbia University Press. p. 6

6. እንደላይኛው ገጽ 9

7. እንደላይኛው ገጽ 68

8. እንደላይኛው ገጽ 62

9. ቼኖዌት፣ ኤሪካ (2014). የህዝባዊ አመጾች ተመሳሳይ ባህሪያትና የአገዛዞች ምላሽ። የፈላጭ ቆራጭነትን የወደፊት ሁኔታን የተመለከተ የአትላንቲክ ካውንስል ፕሮጀክት። አፕሪል 15.
Chenoweth, Erica. 2014 Trends in Civil Resistance and Authoritarian Responses. The Atlantic Council Future of Authoritarianism Project. April 15.

10. ቼኖዌት፣ ኤሪካና ማሪያ ስቴፋን (2011). ሕዝባዊ አመጽ ለምን ውጤታማ ይሆናል? የሃይል አልባ ትግል ስልታዊ ተጠየቅ። ኒው ዮርክ፣ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ። ገጽ 66.

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።

Chenoweth, Erica, and Maria Stephan. 2011. Why Civil Resistance Works: The Strategic Logic of Nonviolent Conflict. New York: Columbia University Press. p. 66

11. ቶማስ ሲ ሼሊንግ (1968). “በህዝባዊ መከታ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎች” በ አዳም ሮበርት እትም ላይ። ሀዝባዊ አመጽ እንደ የሃገር መከታ፡ ሃይል አልባ እርምጃ በጨቋኞች ላይ። ሃሪስበርግ ፔንሲልቬኒያ። ስታክፖል በጽሃፍት ገጽ 304.

Thomas C. Schelling. 1968. “Some Questions on Civilian Defence,” in Adam Roberts, ed., Civilian Resistance as a National Defence: Non---violent Action Against Aggression. Harrisburg, PA: Stackpole Books. p. 304.

12. አከርማን፣ ፒተርና ጃክ ዱቫል (2000)። የበለጠ ሃይል፡ የአንድ ክፍለዘመን የሃይል አልባ ትግል። ለንደን። የቅዱስ ማርቲን ፕሬስ/ፓልግሬቭ ማክሚላን። ገጽ 113-174

Ackerman, Peter and Jack DuVall. 2000. A Force More Powerful: A Century of Nonviolent Conflict. London: St. Martin’s Press/Palgrave Macmillan. pp. 113--174

13. ቼኖዌት፣ ኤሪካና ማሪያ ስቴፋን (2011). ሕዝባዊ አመጽ ለምን ውጤታማ ይሆናል? የሃይል አልባ ትግል ስልታዊ ተጠየቅ። ኒው ዮርክ፣ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ። ገጽ 30-61

Chenoweth, Erica, and Maria Stephan. 2011. Why Civil Resistance Works: The Strategic Logic of Nonviolent Conflict. New York: Columbia University Press. Pp. 30-61

14. እንደላይኛው ገጽ 30-61

15. እንደላይኛው ገጽ 46-49

16. የበለጠ ሃይል፡ ዲሬክትር ስቲቭ ዮርክ። ዮርክ ዚመርማን (2000) ፊልም።

A Force More Powerful. Dir. Steve York. York Zimmerman. 2000. Film.

17. ቢኔንዲክ፣ አኒካ ሎክና ኢቫን ማሮቪች (2006)። ሃይልና የማሳመን ችሎታ፡ ሃይል አልባ ዘዴዎች በሰርቢያ ጸጥታ ሃይሎች ላይ ያደረሰው ተጽዕኖ (2000) እና ዩክሬን (2004)። በኮሚኒዝም ወቅትና ከኮሚኒዝም በኋላ የተደርጉ ጥናቶች 39. ቁጥር 3 (ሴፕቴምበር)። ገጽ 411-429

Binnendijk, Anika Locke, and Ivan Marovic. 2006. Power and Persuasion: Nonviolent Strategies to Influence State Security Forces in Serbia (2000) and

Ukraine (2004). Communist and Post---Communist Studies 39, no. 3 (September). pp. 411---429.

18. ከ ኔቦጅሳ ቾቪች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ፣ ቪሰርኒጅ ኖቮስቲ ኦክቶበር 2, 2010

Interview with Nebojsa Covic, Vecernje Novosti, Oct. 2, 2010.

19. ጋዋንዴ፣ አቱል (2009)። የመመሪያ ማኒፌስቶ፡ ነገሮችን በትክክል መፈጽም። ኒው ዮርክ። ፒካዶር። ገጽ 47

Gawande, Atul. 2009. The Checklist Manifesto: How to Get Things Right. New York: Picador. p. 47

20. እንደላይኛው ገጽ 79

ይህ ምዕራፍ በ Mathew Burrows and Maria J. Stephan (eds.), Is Authoritarianism Staging a Comeback?, Washington, DC: The Atlantic Council, 2015. ታትሞ ወጥቷል።